ሠላሳ አራተኛ ዓመት ቁጥር 38 አዲስ አበባ ሐምሌ 15 ቀን 1967

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት

ነ ጋ ሪ ት ጋ ዜ ጣ

የጋዜጣው ዋጋ	
ባገር ውስጥ በዓመት # 6	በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይታተማል፡፡
ባገር ውስጥ 6 ወር # 3	በሊቀመንበር ጽህፈት ቤት ተጠባባቂነት የወጣ የፖስታ ሳጥን ቁጥር 1031
ባገር ውስጥ ያንዱ #1/2	

ማ ው ጫ

1967ዓ.ም.

የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 17/1967ዓ.ም.

የወንጀል መቅጫ ሥነ ሥርዓት

አንደኛ ሠንጠረዥ ማሻሻያ ደንብ. . . ገጽ 148

የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 17/1967ዓ.ም.

የ1975ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓትን አንደኛ ሠንጠረዥ ለማሻሻል የወጣ ደንብ

‹‹ኢትዮጵያ ትቅደም››

1. አውጫው ባለስልጣን

   በ1954ዓ.ም. በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት በቁጥር 4 ንዑስ ቁጥር /2/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የፍርድ ሚኒስትር ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

2. አጭር ርእስ

   ይህ ደንብ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሠንጠረዥ ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967ዓ.ም. ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

3. ማሻሻያ

   በ1954ዓ.ም. የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሠንጠረዥ ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   በሚከተለው ሠንጠረዥ በመጀመሪያው ዓምድ በተዘረዘሩት የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ የተገለጸውን ማንኛውንም ወንጀል በሶስተኛው ዓምድ ውስጥ በአንጻሩ የተመለከተው ፍርድ ቤት የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

የወንጀል መቅጫ ሕግ ቁጥር **ወንጀሉ** ሰሚው ፍርድ ቤት

310 በበላይ አለቃ ላይ ስለሚደረግ የስድብ ዛቻና የእጅ እልፊት ወንጀል

ንዑስ ቁጥር 1 ---------- ወረዳ ፍርድ ቤት

ንዑስ ቁ. 2---------- አውራጃ ፍርድ ቤት

316 የዘብ ወንጀል

ተራ ክስ (ንዑሥ ቁ.1)---------- ወረዳ ፍርድ ቤት

ከባድ ሁኔታ (ንዑስ ቁ. 2) (መጀመሪያው ኃይለ ቃል)---------- አውራጃ ፍርድ ቤት

ከባድ ሁኔታ (ንዑስ ቁ.2) (ሁለተኛው ኃይለ ቃል) **----------ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

317 የወታደርን ልዩ ትዕዛዝ ስለ መጣስ

ንዑስ ቁጥር 1 ----------ወረዳ ፍ/ቤት

ንዑስ ቁ. 2---------- ወረዳ ፍ/ቤት

ንዑስ ቁ. 3 ---------- ------አውራጃ ፍ/ቤት

319 በዕቃዎች ያለአግባብ ለመጠቀምና ዕቃዎች ስለ ማባከን ---------- አውራጃው ፍ/ቤት

320 የማይገባውን ጥቅም መቀበልና ያላግባብ ስለማጥጥት---------- አውራጃው ፍ/ቤት

335 የህግ ወይም የወል ግደታወችን ስለ መጣስ---------- አውራጃው ፍ/ቤት

354

355

389 የመንግስት ወይም የወታደር ሰነዶች ስለማጥፋት---------- አውራጃው ፍ/ቤት

404 የወታደርን ምስጢር ስለ መግለጽ---------- አውራጃው ፍ/ቤት

418 እስረኛን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ስለመፍታትና

እንዲመልጥ ስለመርዳት ---------- ---------- -------- ወረዳ ፍ/ቤት

421 በአደራ በተሰጠው ዕቃ ያለአግባብ ስለመዘዝ---------- ወረዳ ፍ/ቤት

438 ለፍርድ ባለስልጣን ስለአለመገለጽ---------- ወረዳ ፍ/ቤት

439 አንድ ተከሳሽ ወደ ፍርድ እንዲያቀርብ ስለመደበቅ ---------- ወረዳ ፍ/ቤት

440 የፍርድ ሥራ እንዲሳሳት ስለማድረግ ---------- ወረዳ ፍ/ቤት

444 የፍርድ ሥነ ሥርዓትን ምስጢር ስለመግለጽ ወረዳ ፍ/ቤት

445 ትክክለኛ ያልሆኑትን ወይም የተከለከሉትን የሥራ ማስታወሻወች

በአደባባይ ስለመግለጽ ----------,---------- ወረዳ ፍ/ቤት

449 ስለማነሳሳትና ስለማግባባት አውራጃው ፍ/ቤት

451 የፍርድን ውሳኔ ለማሳሳት በተንኮል ስለሚደረግ የወሬ መግለጽ ሥራ---- አውራጃ ፍ/ቤት

452 በአንድ ወገን ተከራካሪ ጥቅም ላይ የክህደት ሥራ ስለመፈጸም አውራጃ ፍ/ቤት

456 እስረኛ እንዲአመልጥ ስለማደራጀትና እርዳታ ስለማድረግ ወረዳ ፍ/ቤት

488 የእሳት ቃጠሎ አውራጃ ፍ/ቤት

492 በቸለተኝነት የሚደረግ ወንጀል

አንቀጽ 488 የሚመለከት ካልሆነ ---------- **ከፍተኛው ፍ/ቤት**

496 መጠባበቂያ የሚሆን መሳሪያዎች ወይም የሚያገለግልሉትን ዕቃዎች

ማጥፋት ወይም አለማደራጀት---------- ወረዳ ፍ/ቤት

506 ውሃን ስለማበላሸት አውራጃ ፍ/ቤት

514 አልኮል ወይም እስፒርቶ ያለባቸውን መጠጦች በማይገባ ስለመስጠት ወረዳ ፍ/ቤት

515 አእምሮን በሚነኩ ሥራዎች አደጋ ስለማድረግ ወረዳ ፍ/ቤት

516 ሥራይ በሚሆኑ ወይም ይህን በመሳሰሉ ነገሮች በሰው ላይ

አደጋ ስለማድረግ----------ወረዳ ፍ/ቤት

517 ከባድ ሁኔታወች ወረዳ ፍ/ቤት

561 ቅጣቱን የሚያከብዱ ሁኔታዎች 558-560 አውራጃው ፍ/ቤት

571 መኖሪያ ቤትን ስለመድፈር ወረዳ ፍ/ቤት

572 ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች ወረዳ ፍ/ቤት

589 የመድፈር ሥራ አውራጃ ፍ/ቤት

590 በንጽሕና ክብር ላይ ስለሚደረግ የኃይል ተግባር አውራጃ ፍ/ቤት

591 ለመቃወም በማይቻሉ አእምሮዋቸው በተበላሸ ወይም የአእምሮ ደካማ

በሆኑ ሰዎች ክብር ንጽህና ላይ ስለሚደረግ የድፍረት በደል---------- አውራጃ ፍ/ቤት

592 በሆስፒታል ውስጥ በተገኙ ሰዎች በታገዙ ወይም በታሠሩ ሰዎች

ክብር ላይ ስለሚደረግ በደል ---------- አውራጃ ፍ/ቤት

594 በህጻናቶች ክብረ ንጽሕና ላይ ስለሚደረገው በደል አውራጃ ፍ/ቤት

598 ከባድ ሁኔታዎች አውራጃ ፍ/ቤት

600 ለተፈጥሮ ግብር ተቃራኒ የሆነ የአመንዝራነት ሥራ አውራጃ ፍ/ቤት

601 ቅጣቱን የሚያከብዱ ሁኔታዎች አውራጃ ፍ/ቤት

605 ሴቶችንና አካለመጠን ያልደረሱትን በማቃጠር በማከራየት ስለማነገድ----- አውራጃ ፍ/ቤት

606 ስለከባድ ሁኔታዎች አውራጃ ፍ/ቤት

609 ንፍረተ ነገርን የሚያሳዩ ወይም ለመልካም ጠባጥ ተቃራኒ የሆኑትን

ነገሮች አሳትሞ ስለ ማውጣት ---------- አውራጃ ፍ/ቤት

630 ስለ ስርቆት ወረዳ ፍ/ቤት

631 የሥራ ኃይልን ስለ መስራት ወረዳ ፍ/ቤት

632 የጋራ የሆኑትን ዕቃዎች ስለመስራት ወረዳ ፍ/ቤት

633 በሙታን ላይ ስለሚሠራ የስርቆት ወንጀል ወረዳ ፍ/ቤት

635 ከባድ ስርቆት አውራጃ ፍ/ቤት

641 እምነት ስለማጉደል አውራጃ ፍ/ቤት

642 ከባድ የሆነ የእምነት ማጉደል አውራጃ ፍ/ቤት

654 ከባድ ሁኔታ አውራጃ ፍ/ቤት

663 በግል ሰው ጥቅም ላይ የተደረገ የተንኮል ሥራ አመራር አውራጃ ፍ/ቤት

664 ከባድ የሆነ ተንኮል ያለበት የሥራ አመራር አውራጃ ፍ/ቤት

በሌላ ሕጐች ስለ ተወሰኑ ቅጣቶች

© ቅጣቱ **ከአምስት ዓመት** የማይበልጥ እሥራት

መቅጫ ሳይኖረውም ወይም ከነመቀጫው ሲሆን---------- --- ወረዳ ፍ/ቤት

© ቅጣቱ **ከአስር ዓመት** የማይበልጥ እሥራት መቀጫ ሳይግረውም ወይም

ከነመቀጫውም ቢሆን---------- አውራጃ ፍርድ ቤት

© ቅጣቱ ከዚህ በላይ ከተመለከተው የሚበልጥ ሲሆን ---------- **ከፍተኛው ፍ/ቤት**

4. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል

አዲስ አበባ ሐምሌ 15 ቀን 1967 ዓ.ም.

አማኑኤል ዓምደ ሚካኤል

የፍርድ ሚኒስትር